# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ሠራተኛ፡ገበሬ፡ነጋዴ፡ወታደር፡ምሁር— መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም፡፡

ቁጥር 21

ቀን 21.5.67


## ወሬት ቢያገበሩት ወንጅ አይሆንም፡፡

ደርጉ የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም ብሎ የጠራውን መመሪያ ካስታወቀ ይኸው ወር ሆነው፡፡ አንዳንዱ የዚህን መመሪያ መንፈስ የተከተሉ እርምጃዎች በመውሰድ የሶስት ባንኮችንና የጥቂት ኢንሹራንስ ኩባንያዎችን ባለቤትነት ወደመንግስት ካዛወረም ሰነበተ፡፡ የሰፊውንም ሕዝብ በዝበዛ በደልና ጭቆና፡የሰፊውን ሕዝብ በመሳፍንትና በኢምፔሪያሊዝም መረገጥና መበጨቅ በኘሮፓጋንዳ መሳሪያዎቹ ሲገለጽ ቆይቶአል፡፡ ወታደራዊው መንግስት ለሰፊው ሕዝብ የቆመ፡ሰፊውን ሕዝብ ለማገልገል የተነሳ፡ለሕዝቡ መብቱን ሊመልስ የቀረጠ መሆኑ በመደጋገም ተገልጾአል፡፡ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መብት በከፊል መመለሱ፡ከጢቂቶቹ ብሄሮች አንዱ የሆነው የኦሮሞ ብሄር ቋንቋ በመጠኑ ማእረግ ማግኘቱ ይህንን የመብት መመለስ መንገዱ የጀመርን መሆኑን ያሳምን ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በሚነገረውና በሚደረገው መካከል ከፍ ያለ ልዩነት ይታያል፡፡ በመጀመሪያ መታየት ያለበትን የመሬቱን ጉዳይ የወሰድን እንደሁ በቀርቡ ህግ ይወጣል ከተባለ ወራት በወራት ተተክተው ሲሄዱ ህጉ አለመውጣቱን እናያለን፡፡ ህጉ እንኳን ቢዘገይ ለህጉ መሰናዶ ሊሆን የሚገባው የጭሰኛውና የአነስተኛው ገበሬ የመደራጀት መብት እስካሁን ተነፍጉ ይታያል፡፡ በመጠኑም ቢሆን ከዚህ በፊት ተደራጅተው የነበሩ የአንዳንዱ አውራጃ ጭሰኛና አነስተኛ ገበሬዎች እየተገናኙ በችግራቸው ላይ እንዳይወያዩና ለችግራቸውም መፍትሄ እንዳይፈልጉ በደርግ ተወካዮች ታግደዋል፡፡ መሬት ሳራሹ በላችሁ ተናገራችሁ፡ባለርስቱን አስቀየማችሁ በመባል ከየካቲት ጀምሮ በፀረሕዝቡ በአንዳልካቸው መንግስትና ከመስከረምም ወዲህ በተቋቋመው ወታደራዊ መንግስት የታሰሩት ጭሰኞችና ተማሪዎች አሁንም በየእስር ቤቱ ይማቅቃሉ፡፡

ከፍተኛ ባለርስቶች፡ባላባቶች፡-ሕዝቡን የሚያወናብዱ ገፋፊ ቃልቻዎችና ባለዛሮች አንዳንዱ የቤተክርስቲያንና የመስጊድ መሪዎች እንደልባቸው ቀሚያቸውን ሲቀጥሉ ይታያሉ፡፡ ጭሰኛውና ድሃው ገበሬ መሬት መሬት እያለ ሲጮህ እነኚህ አወናባጆች መሳሪያ እያከማቹ፡አሽከር እየቀጠሩ ለጦርነትና ለሽፍትነት ሲዘጋጁ ይታያሉ፡፡ ባላባትነታቸውንና የሃይማኖት መሪነታቸውን እያስታከኩ ሕዝቡን ለመከፋፈል በየአደባባዩ በየገበያው ሲሰብኩና ሲያስሰብኩ ውስጥ ውስጡን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ከአልጋወራሽ አስፋወሰን፡ከዘውዱ ገብረስላሴ፡አገራቸውን ከከዱት የአጼ አምባሳደሮች ጋር፡ከተራማጆች ጠላት ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና ከሱቸሎቹ ከነሳውዲው ፋይሳል ጋር ሲላላኩ ይታያሉ፡፡ በቸልተኝነት ያመለጡት እነመንገሻ ስዩም፡እነነጋ ተገኝ በቤገምድርና ስሜን፡በትግራይ በወሎ፡በጐጃም በሸዋ ከሚገኙት መሰል ወገኖቻቸው የሕዝብ ተባዮች ጋር አሁንም በመደለት ላይ ይገኛሉ፡፡ ሕዝባዊውን ንቅናቄ ለማኮሸፍ የማይሞክሩት ሴራ የለም፡፡ ቢትወደድ አሊ ሚራህም ረሃብ የጨረሰውን ያደቀቀውን የአፋርን ሕዝብ አሁንም ለመበዝበዝ እንዲያመቸው ከመንገሻ ስዩምና ከሳውዲ አረቢያ ጋር በመላላክ ለመሸፈት ይዘጋጃል፡፡ በላቸው ጀማነህም ከነዚህ አድሃሪ ወገኖችና ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር በመመሳጠር የአሁኑን መንግስት ገልበጦ የኢምፔሪያሊስት ጥገኛ መንግስት ለማቋቋም ልዩ ልዩ የዘገጁት ሴራዎችን ከመጠንሰስ አልተቆጠበም፡፡ እነኚህና ሌሎችም የሕዝብ ጠላቶች ቀደም ብለው እንዲያዙ ከመወትወት ባንቆጠብም እስካሁን ድረስ ምንም አይነት እርምጃ አልተወሰደባቸውም፡፡ እንዲያውም አንዳንዶቹ ከብርና ሞገስ አልተነፈጋቸውም፡፡እንደጅማው ባላባት ይህንን ያህል ጋሻ ለድርቅ ሰጠን እያሉ የሚያፈዙም አሉ፡፡ በጠቅላላው መሬትን ለአራሹ ልሰጥ ነው ከሚል መንግስት የማይጠበቅ ተባዮችን የማባበል፡እንደልባቸው የመልቀቅ፡እንዲረቡ እንዲሰቡና ሕዝቡን ለመውጋት እንዲዘጋጁ ፋታ የመስጠት ሁኔታ በሰፊው ይታያል፡፡

ስለገበሬው ካነሳን ዘንዳ ሌላ የሚያስገርም ድርጊት በንግድ ሚኒስቴርና በአንዳንድ የደርጉ ተወካዮች ተዘጋጅቶ የታወጀው የዋጋ ቁጥጥር ጉዳይ ነው:: የዋጋ ቁጥጥር የሰፊው ሕዝብ ወገን ነኝ በሚል መንግስት ሲታወጅ ሰፊውን ሕዝብ/ጭሰኛውንና ትናንሽ ገበሬውን፡ላብአደሩን፡ ዝቅተኛ የቢሮ ሰራተኛውን፡አስተማሪውን፡ተማሪውን፡አነስተኛ ነጋዴውንና ወታደሩን/ የሚጠቅም መሆን ነበረበት:: ነገር ግን የዋጋ ቁጥጥር ተብሎ የተገለፀው ዋጋ ከብት አርቢውን፡ከብት ቀላቢውን፡ አራሹን ገበሬ፡አነስተኛውን ነጋዴ፡ወዘተ. የሚጎዳ ሆኖአል:: ለምሳሌ የስንዴ ዋጋ ከመወሰኑ በፊት በሸዋና በአሩሲ ነጋዴው ከገበሬው ኩንታሉን ስንዴ በአስራ ስድስትና በአስራ ሰባት ብር ገዝቶ በአዲስ አበባ ገበያ ላይ በሃያ ሶስትና በሃያ አራት ብር ይሸጥ ነበር:: አዲሱ የዋጋ ውሳኔ ከመጣ ወዲህ ግን ያንኑ እህል ነጋዴው ከገበሬው ላይ በአስራ ሁለትና በአስራ ሶስት ብር ይገዛል:: ብዙ ጋሻ መሬት በዘመናዊ ዘዴ አርሶ ብዙ ሺህ ኩንታል አምርቶ የሚሸጠው ሃብታም ገበሬ/የገጠር ዲታ/ እህሉን በጅምላ ለትላልቅ ወፍጮ ቤቶች ስለሚሸጥና ከመሰለውም እህሉን በመጋዘኑ አስቀምጦ ደህና ዋጋ ስለሚጠብቅ ምንም ያህል አይጎዳም:: አነስተኛው ገበሬ ግን ዋጋ ቢጨመረም ተቀነሰ ከላይ እስከ ታች ከተረበረቡበት ነጋዴዎች ገፈፋ ስለማይድንና የአሁኑም ዋጋ ቅናሽ ሙሉ በሙሉ በቀጥታ በአርሱ ትከሻ ላይ ስላረፈ ክፉኛ ተጎድቶአል፤ ቀን ወጣልህ እየተባለ ከስርአል::

ሌሎቹም የግብርና ምርት ዋጋዎች ይኸው ናቸው:: የሚጠቀሙት የከተማውን ደሞዝተኛና የከበርቴውን ክፍል ብቻ ነው:: እንዲያውም ይህ ውሳኔ ሰፊውን ሕዝብ በገጠሬና በከተሜ ይከፋፍለዋል:: የዋጋው መወሰን የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም መጠበቅ ነበረበት:: የከተሜው ቀለብ እንዳይጓደል መንግስት አስቀድሞ ንግዱን በቁጥጥሩ ስር ማግባት ነበረበት:: የደርጉ አገዛዝ ሕዝብን ለመጨቆን ያዘጋጃቸው እንደእህል በርድና እህል ማህበር የመሳሰሉ ድርጅቶች ለሕዝቡ እንዲሰሩ መደረግ ነበረባቸው:: ይህ ሳይሆን ቀርቶአል::ለሰፊው ሕዝብ ህልውና በጣም አስፈላጊ በሆኑት በምግብ በልብስ ወዘተ. ላይ የዋጋ ውሳኔና ቁጥጥር መደረጉ በመሰረቱ ትክክል ነው:: ዋጋ በሚወሰንበት ጊዜ ግን አዲሱ ዋጋ የገበሬውንም ሆነ የላብአደሩን ጉልበት እንዳያራክስበት፡ሰፊውን ሕዝብ ወደባሰ ችግር እንዳይከተተው ሰፊ ጥናትና ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ አሁን እንደተደረገው የእህል ዋጋ ተቀንሶ የስንዴ ዱቄትና የዳቦ ዋጋ ሳይነካ መቅረቱ የጠቀመው ባለትልልቅ ወፍጮ ቤቶችንና ዳቦ ጋጋሪዎችን ነው::

የዋጋ ቁጥጥር ዋና አላማው አፈርገፊው አነስተኛ ገበሬ እንዳይጎዳ፤ እንዲሁም ዝቅተኛ ገቢ ያለው ከተሜ እንዳይጎዳ፤ ነጋዴዎች ከገበሬው የሚገዙበትን ዋጋ ዝቅ በማድረግና ለተጠቃሚው የሚሸጡበትን ዋጋ በጣም ከፍ በማድረግ ከልክ በላይ የሆነ ትርፍ እየዛቁ ሰፊውን ሕዝብ እንዳይበዘብዙ ለማድረግ ነው:: በመሰረቱ ነጋዴዎችም ትርፋቸው ከልክ በላይ እንዳይሆን ማድረግ ነው እንጂ ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች እስከሆኑ በመጠነኛ ንግድ ውስጥ እስከተሰማሩ ድረስ የንግዱን ስራ ለመቀጠል የሚያበቃቸው መጠነኛ ትርፍ ማግኘት እንደሚገባቸው ማወቅ ያስፈልጋል::

በተጨማሪም የዋጋ ቁጥጥር ያለበቂ ጥናት በአንድ ጊዜ በሁሉም እቃ ላይ ሊደረግ አይቻልም:: ምክንያቱም የዋጋ ጉዳይ ከረቂቅ የኢኮኖሚ አሰራር ህግጋት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው:: የእያንዳንዱን እቃ ዋጋ ለመቆጣጠርና በተለይም ዝቅ ለማድረግ የሚቻለው በጠቅላላው የእቃውን እጥረት ለማስወገድ ሲቻል ነው:: በአንድ ጊዜም በችኮላ ሊከናወን አይችልም::

እነዚህን ጉዳዮች በሙሉ ባለመገንዘብ አሁን እንደተደረገው የኢኮኖሚን አሰራር ህግጋት የማይከተል የእቃዎች ዋጋ መታወጁ በከተማው የእቃ እጥረትን በመፍጠር ለሕዝቡ ችግርን ለመንግስትም ጥላቻን ያተርፋል:: ይህንንም በመመልከት ነው የሰሞኑ የዋጋ ቁጥጥር መሰረቱ ምን እንደሆነ የምንጠይቀው:: ያም ሆነ ይህ ቁጥጥሩ በኢኮኖሚ ጥናት ላይ ያልተመሰረተ፡ከአርሻም ሆነ ከገበያ ጋር ግንኙነት ያላቸው ድርጅቶች ያልመከሩበት፡ምስኪኑ አፈርገፊ ገበሬ ይጠቀመው እንደሁ፡ይጎዳው እንደሁ ያልተጠየቀበት፡ምናልባትም ያው መንግስቱ ወዳጅና ጠላትን ባለመለየት በሚመርጣቸው አድሃሪ አማካሪዎች እርሱኑ መልሰው ለማጥላላት ያቀዱት የአድማ ድርጊት ይመስላል::

ሌላው የገጠሩ አጣዳፊ ችግር የድርቁ መስፋፋት መሆኑ ግልጽ ነው:: ይህን መቋቋም ለሃገሪቱ ዋና ጥያቄ ነው፤ የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ ነው:: ታዲያ በዚህም አቀጣጫ ቢሆን የሚታየው ብዙ ፕሮፓጋንዳና ትንሽ ስራ:ትንሽ ውጤት ነው:: የመቋቋሚያው ስራ ችላ ተብሎአል፤ ተዘንግቶአል:: እርዳታ ሰጭዎቹም ሆኑ የእርዳታ ሰብሳቢው ድርጅት አድሃሪ እንደመሆናቸው መጠን እርዳታውን እንደምጽዋት ስለሚቆጥሩት ሕዝቡ ራሱን በራሱ እንዲያድን ምንም ሙከራ አላደረጉም:: ይህን ቀደም ብለን በዚሁ ጋዜጣ በሰፊው አብራርተናልና አንመለሰበትም::

በሌላውስ በኩል ቢሆን የሕዝቡን ጥቅም ለመጠበቅ ምን ጥረት ተደርጉአል ብንል ያንኑ -በሚነገረውና በሚሰራው መካከል ያለውን ከፍ ያለ ልዩነት እናያለን:: ተራማጆች በእስር ቤት ይማቅቃሉ:: እነሻለቃ ተፈራ ተክለአብ:እነዶክተር አሸቱ ጪሌ:እነኮሎኔል አምሩ ወንዴ:እነአቶ ዘውዴ በዳዳና ሌሎችም የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ለሰፊው ሕዝብ ተቆርቋሪነታቸው በግልጽ እየታወቀ በእስር ቤት ውስጥ ሲማቀቁ የሃይለስላሴ መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣኖችና የመሳፍንት ወገኖች 'በርእሰ ብሄሩ ምህረት ተደርጉላቸው' ተለቀቀዋል:: የኢ.ዩ.ተ.ማ. መሪዎች ተይዘው መያዛቸው እንኳን አልተገለጠም:: አባሎቻቸውን ወክለው የተነሱት የኤሰአማ መሪዎች ከሳቸው እንኳን አልተነገራቸውም::አስራ ሶስት የገንዘብ ሚኒስቴር ሰራተኞች ከሳቸው አሁንም በቀጠር ተራዝሞአል::

ስለሕዝብ በተነሱ ወገኖቻችን ላይ ይህን በደል ማድረሱ ምን ይባላል? በሌላ በኩል ደግሞ ሰራተኛው እንዲደራጅ:እንዲሰበሰብ:እንዲመካከር መብቱ አልተጠበቀለትም:: በአንድ በኩል ሶሻሊዝም እየተባለ እየተለፈፈ በሌላ በኩል የአሜሪካ የስለላ ድርጅት/ሲአይኤ/ የኢሰአማን መሪዎች ለመግዛት ገንዘቡን ያፈስሳል:: አማካሪ አሰልጣኝ እያለ የሚልካቸው ሰላዮቹ ሲሚናር ያዘጋጃሉ:: ስለሶሻሊዝም:ስለሰራተኛ መብትና ጥቅም:ስለትግሉ አመራር ተራማጆች እንዳያስተምሩ:እንዳያደራጁ ተከልክለው ተይዘዋል::የቀንደኛው ሰላይ የበላቸው ደማነህ ቱልቱላዎች አረፋ:እጅ እግራችሁን አጣምራችሁ የምንለፍፍላችሁን ብቻ አዳምጡ ይሉናል::

ቀደም ብሎ በተያዘው መስመር በመቀጠል ደርግ ተዋናይ:ሕዝብ ተመልካች ስለሆነ ትእይንቱ ሲከታተል ሕዝብ እንዲያጨበጭብ ይጠየቃል:: ለውጥ ከላይ ወደታች:ከአስተዳዳሪ ወደሕዝብ ይመጣል:: አርፋችሁ ተቀመጡ:የመሬት ህግ ይታወጃል እያሉ የደርግ ተወካዮች በየገጠሩ ያስረዳሉ:: የእድገት በህብረት ዘማቾች ለሕዝቡ የፖለቲካ ትምህርት እንዳይሰጡ ለራሳቸውም ቢሆን ምንም አይነት ገለፃ ሳይደረግላቸው ቀርቶአል::መንግስቱ የሚጠነቀው ከአድሃሪዎች ማለት ከኢምፔሪያሊስቶች ሬዲዮ ጣቢያዎች/በስራተ ወንጌል:ጀርመን ሬዲዮ:ቢቢሲ:የአሜሪካ ድምጽ:ዐዘተ./ ከፊውዳል ጪቆኖች ለሚወረወረው ሂስ ነው::

ይህ ሁሉ እንዴት ሊሆን ቻለ? ከዚህ በፊት እንደገለጸነው በደርጉ ውስጥና በደርጉ አካባቢ አድሃሪ ሃይሎች የሕዝቡን እንቅስቃሴ ለማክሸፍና ወደ ሂላ ለመመለስ የማያደርጉት ሙከራ የማያጠምዱት ሴራ የለም:: በቀንደኛው ሰላይ በበላቸው ደማነህ መሪነት:በመሃረነ ምንዳ:በደምሴ ተፈራ:በሽመልስ አዱኛና በተካልኝ ገዳሙ:በአንዳንድ የፖሊስ ንኡስ ደርግ አባሎች በተለይ በሻለቃ እንየው አዝማችነት የማወናበድ ስራቸውን ቀጥለዋል:: በአድራጉታቸው የሲአይኤ ገንዘብና የምክር ድጋፍ እንዳለና ከደርጉም ውስጥ የነዚህ ሰዎች የሴራ ባልንጀሮች እንዳሉበት ግልጽ ነው:: የሚከተሉት እስትራተጅም እንደሚከተለው ነው:: ለአዲሱ አስተዳደር ቁልፍ የሆኑትን ቦታዎች: የክፍለ ሃገሩን አስተዳደር:የአውራጃውንና የወረዳውን አስተዳደር በሰዎቻቸው ይሞላሉ:: በእፋቸው የለውጡ ደጋፊዎች በመምሰል በመንግስት የተያዙትን ፋብሪካዎች፡ የእርሻና የንግድ ድርጅቶች 'በተማሩ ወጣቶች' አስያዘን እያሉ አድሃሪነታቸው የታወቀውን ሰዎች በነዚህ ስፍራዎች ይተካሉ:: ለምሳሌ አደሩን የብሄራዊ ሃብት ልማት ሚኒስቴር በሚኒስትርነት:በቋሚ ተጠሪነት:በመምሪያ ሃላፊነት ያስያዙት ከጥቂቶች በስተቀር/ለአይን ያህል/ በአድሃሪዎች ነው:: እንዲያውም በዱሮው መንግስት እንኳን በሌብነት የተገለሉትን እንደነዶክተር ጥላሁን አይነቶቹን ከፍ ያለ ስልጣን ሰጥተዋቸዋል::

ወጣትነትና መማር ለተራማጅነት ምስክር ወረቀት አለመሆኑ ሲታወቅ የዲግሪ ጋጋታ በመቁጠር የዋህ የሆነውን አንዳንድ አገርወዳድ ሊያታልሉ ይሞክራሉ:: ሁለተኛው ዘዴያቸው

በሚኒስትሮች ምክር ቤትና በደርጉም ውስጥ ጭምር ባሉአቸው ቡችሎች አማካይነት የተዘጋጀው የመሬት
ይዞታ ህግ እንዳይፀድቅ:ከፀደቀም ስራ ላይ መዋሉ እንዲዘገይ ይጥራሉ::ጥቃቅን ነጥቦችን አጧም
መው በመተርጎም እንዳለካቸው በሸማቸው ስራ የማይችሉ ሚኒስትሮች እየተረዱ መስተ ሊወርዱ ነው፤
የለውጥ አለማችን ሊጨናገፍ ነው፤ የኤርትራ ችግር ሳይፈታ አይሆንም፤ ጉሳ ለጉሳ ወገን ለወገን
ሊዋጋ ነው እያሉ ከዋናው ጉዳይ ጋር ራቅ ያለ ግንኙነት ያላቸውን ጉዳዮች በመቀስቀስ ይህንን
ህግ ለማቆየት ይጥራሉ::በተለይ የሚያተኩሩት ስለደርጊት በሚነሳው ጉዳይ ላይ ነው:: ገበሬው
ከተደራጀ:ተደራጅቶም ከሳብአደሩ ጋር ከተባበረ:ከተራማጅ ሃይሎችም ጋር ከገጠመ የአድሃሪያች
መጥፊያ ቀን መቃረቡን ስለሚያውቁ የደርጊትን መሬቀድ በተቼበረበረ የፀጥታ ሪፖርት ላይ እያስመ
ረኮዙ አደገኛ ነው:ሕዝቡ ቀደም ይማር:ጠላቶቻችን ተጠናክረዋል እያሉ በደርጉ ውስጥና በአካባቢው
ያሉትን የተራማጅ ወገኖች ያወናብዳሉ::

ሶስተኛው ዘዴያቸው የሳቦታጅ ዘዴ ነው:: ከላይ እንደጠቀስነው 'የኢትዮጵያ ትቀ
ደምን አሳማ' ተቃውሞአል እያሉ የገጠሩንና የከተማውን ተራማጅ ያሳስራሉ:: ይህም የሚደረገው በደ
ርጉና በሕዝቡ መካከል መቃቃር እንዲፈጠር ነው:: በበዙ ክፍለሃገሮች እንደተደረገው መሬት
ላራሹ የሚሉትን ተራማጆች ማስፈራራት በደርጉ አባሎችና በንኡስ ደርጎች እንዲስፋፋ ያደርጋሉ::

አራተኛው ዘዴያቸው ከተራማጆች ቀደመው ይበልጥ ለውጥ የሚፈልጉ በመምሰል ያልተጠና
የችኮላ እርምጃ እንዲወሰዱ ያደርጋሉ:: ከላይ እንዳስረዳነው የዋጋው ቁጥጥር ጨዋታ ይህን የሚ
መስል ነው:: እንዲሁም በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች ሳይወሰዱ ለመንግስት ለጊዜው
ብዙ ጥቅም የማይሰጡ የማያዋጡ የንብረት መውረስ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ይገፋፋሉ:: በንግድ
አለም የጊዜው ዋና ጠላቶች የኢምፔሪያሊዝም ቀጥያ የሆኑ አቀባባይ ነጋዴዎች ሲሆኑ መንግስቱ በአ
ነስተኛ ከበርቴዎች ላይ እንዲያተኩር ይገፋፋሉ:: ትልቀን ተቶ ትንሹን:አደገኛውን ተቶ ደካማውን:
ጠላቱን ተቶ ወዳጁን እንዲያጠቃ ይመክራሉ፤ ያዛሉ ይወስናሉ:: ሰሜን ከደቡብ:እስላም ከክርስቲ
ያን:ብሄር ከብሄር እንዲጋጭ ይጥራሉ:: በፖሊስ:በበሄራዊ ጦርና በአንዳንድ የጦር ሃይሎች ክፍ
ሎች ውስጥ ወሬ በማሰራጨት:ሕዝብ የሚያስቀጣ ድርጊት በመፈፀም ደርጉን ወደፋሺዝም ይገፋፋሉ::

እንግዲህ ከዚህ ሁሉ የምንረዳው አድሃሪ ሃይሎች በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም መሪነት:
በበላቸው ጀማነህና በግብረአበሮቹ ግንባር ቀደምነት:በደርጉ ውስጥና በአካባቢው ባሉ ባለስልጣኖች
ደጀንነት በሕዝብ ንቅናቄ ላይ መዘመታቸውን ነው:: በደርጉ ውስጥ ያሉ ተራማጆችና በጠቅላላውም
የሕዝብ ወገን የሆኑ አገርወዳዶች መገንዘብ ያለባቸው ከዚህ በፊት ደጋግመን እንደተናገር ነው
ትግሉ በገፈኛው ንጉስ መያዝ ወይንም በጥቂት አምባገነን መኳንንት መገደልና በንብረታቸው መወረስ
የሚቆም አለመሆኑን ነው::መዘንጋት የሌለባቸው ትግሉ የሚቀጥልና ገና የሚፋፋም መሆኑን፤ በሰባት
ወይም መቶ የጦር ሃይል አባሎች ብቻ ሊካሄድ የሚችል አለመሆኑን፤ ንቅናቄውን ሰፊው ሕዝብ ራሱ
መምራት እንዳለበትና ንቅናቄውም ከዳር የሚደርሰው ትክክለኛና ያልተዘባረቀ መሪነት ሲያገኝ መሆ
ኑን ነው::አድሃሪ ሃይሎች በኢምፔሪያሊስቶች እርዳታ በውጭና በውስጥ ይደራጃሉ::የብሄሮችም
ጥያቄ በተለይ የኤርትራው ጉዳይ የኤርትራውያን መብት በሚገባ ታውቆ:ከፍፁም እኩልነትና ከወንድ
ማማችነት አንፃር ሕዝቡ ራሱ በሚፈቅደው መንገድ ሊፈታ ሲገባው ልዩ ልዩ ሰንካላና አድሃሪ ሃሳብ
በማቅረብ ሰላማዊ መፍትሄ እንዳያገኝ ይጥራሉ:: መንግስቱ ውስጥ ገብተው ተንሰራፍተው በመቆጥ
የመንግስቱን የቢሮክራሲ መኪና ለተንኮላቸው ያውላሉ::

በዚህን ጊዜ በደርጉም ውስጥ ሆነ በውጭ የሚገኙ ተራማጆች ምን ማድረግ አለባቸው?
በመጀመሪያ የንቅናቄውን ወዳጆችና ጠላቶች መለየት አለባቸው:: የንቅናቄውን ወዳጆች —ለረጅም
ጊዜ ኢምፔሪያሊዝምንና ባላባታዊ አገዛዝን ሲቃወሙ የቆዩትን ተራማጆች— ማስጠጋት መሰብሰብና
እንዲደራጁ መፍቀድ አለባቸው፤ ለሰፊው ሕዝብ የመደራጀት መብቱን መፍቀድና የፖለቲካ ሀሳቡን
ከፍ እንዲያደርግ ማበረታታት አለባቸው::አድሃሪዎችን ከስልጣንም ሆነ ከምክር ቦታ አካባቢ
ያለማመንታት መንቀል አለባቸው::እነዚህንም በአገርወዳድነት:በተራማጅነት:በስራ ችሎታ ብቻ
በተመረጡ ሰራተኞች መተካት አለባቸው::የታሰሩ ተራማጆች እንዲፈቱ መወትወት እንዱ የነኘሀ

በደርጉ ውስጥና ውጭ ያሉ ተራማጆች ተቀዳሚ ተግባር ነው:: የነርሱ መፈታትም በተራማጆች መካከል ሊፈጠር የሚችለውን የመደጋገፍ ሁኔታ ሊያበስር እንደሚችል ማስረዳት የሁላችንም ተግባር ነው:: የመሬት ህግ ያስማገኛ: ያለማድበስበሽና መንፈሱን የሚሸር ለውጥ ሳይደረግበት በስራ ላይ የሚውል አይነት ሆኖ እንዲታወጅ መገፋት ሌላው የተራማጆች ግዴታ ነው::በተለይ በደርጉ ውስጥ የሚገኙ ተራማጆች ወዳጅና ጠላታቸውን ለይተው ማወቅና ብርቱ ጥንቃቄም ማድረግ ይኖርባቸዋል::ከአድሃሪ ሃይሎች ጋር ተከሻ ለተከሻ እየተሻሹ መቀጠል እንደማያዋጣቸው ተረድተው ከነርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማቋረጥና ከተራማጆች ጋር ለመተባበር መጣር ያስፈልጋል:: ተራማጆችም ደጋግመው በጠየቁት መሰረት የታሰሩትን ተራማጆች መፍታት: የሰፊውን ሕዝብ መደራጀት መፍቀድና ማበረታታት:ከሌሎች አገሮች ታሪክም መማር ይኖርባቸዋል:: የነበርን ጅራት አይይዙም ከያዙም አይለቁም እንደሚባለው አድሃሪያችን ነካክቶ ሳያጠፉ መቈጥ እንደማይቻል ይረዱ::ከወዳጆቻቸው ከተባበሩ ድል ያደርጋሉ፣ ከጠላቶቻቸው ጋር ከሰነበቱ ይጠፋሉ::

የመደብ ጠላታችንን እንለይ
ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል::